Australian Government

# ስለ ኮሮና ቫይረስ/Coronavirus (COVID-19) እምነትና የተሳሳተ መረጃ

## ውሸት: በአንቲባዮቲክስ/antibiotics ወይም በጸረ-ወባ/antimalarial መድሃኒቶች ለኮሮና ቫይረስን/ coronavirus ማዳን ትችላለህ

**እውነት:** እስካሁን ለኮሮና ቫይረስ/coronavirus ክትባት ወይም ህክምና የለም።

በዓለም ዙሪያ ያሉት ተመራማሪዎች ለቫይረስ መከላከያ ክትባት ለመፍጠር በጣም እየሰሩ ሲሆን ነገር ግን ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ አናውቅም። ግምቱ ከ12 ወይም 18 ወራት ባለው ጊዜ ይሆናል።

እንዲሁም ተመራማሪዎች ለኮሮና ቫይረስ ህክምና ሊረዳ ይችላል ያሉትን የተለያዩ መድሃኒቶችን መጠቀም ማለት የቁርጥማት፣ ጸረ-ወባ እና የሄች አይቪ/ HIV መድሃኒቶችን ያካተተ መድሃኒቶችን እየተከታተሉ ነው። ለኮሮና ቫይረስ አያድኑም ነገር ግን በቫይረሱ ለሚያዝ የሰው ቁጥር እና ከባድ ችግሮችን ሊቀንስ ይችላል።

ስለዚህ ለኮሮና ቫይረስ ክትባት ወይም ህክምና ላለመጠበቅ፣ ይህ ጠቃሚ ሲሆን – ታዲያ ለዚህ ነው በአውስትራሊያ በጣም ብዛት ያለው የህዝባዊ ጤና እርምጃዎች የወጣው።

## ውሸት: ህጻናት የኮሮና ቫይረስ 'ከፍተኛ አሰራጮች' ናቸው

**እውነት:** በአጠቃላይ ህጻናት ለጀርምና ትላትል 'ከፍተኛ አሰራጭ' እንደመሆናቸው ቢታወቅም፣ በእርግጠኝነት ለኢንፍሎዌንዛ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ይህን ከኮሮና ቫይረስ ጉዳይ ጋር ማየት አይገባም። ቢያንስ እስካሁን አልታየም። የዚህ ቫይረስ አብዛኛው ስርጭት በህጻናት ላይ ይከሰታል የሚል በዚህ ዓለም ውስጥ በየትኛውም ቦታ የሚያሳይ ጥሬ መረጃ የለም። ይህንን አልተቆጣጠርንም። ለሆን ይችላል፣ ነገር ግን መረጃዎች ሁሉ እንደሚያሳዩት ህጻናት የኮሮና ቫይረስ ከፍተኛ አሰራጭ እንዳልሆኑ ነው።

## ውሸት: አውስትራሊያ በቂ የህክምና መሳሪያ እና አቅርቦት (የንጹህ አየር ማስገቢያ መሳሪያ/ventilators፣ ጭምብላ፣ የመመርመሪያ እቃዎች) ልታገኝ አልቻለችም

**እውነት:** ቀላሉ መልእክት ለታካሚዎች እና በቁርጥ ቀን ለእነሱ ለሚንከባከቡ የጤና ሠራተኞች ከሆነ – አዎ፣ ይህንን ወረርሽን ለመዋጋት በቂ መሳሪያ እንዳላት ነው። ይሁን እንጂ ከሁሉም ምርመራ አቅርቦት ጋር በተዛመደ ውጥረት እንዳለ ምክንያቱም በዓለም ላይ ከፍተኛ የመገልገያ ጥያቄ እየጨመረና የማምረት አቅም ሳቢያ ነው።

ለግላዊ መከላከያ መሳሪያ የሚሆን ሁልጊዜ እየመጣ ስለመሆኑ ሰራተኞች ማረጋገጥ ይችላሉ። ይህ ማለት፣ በተዘዋዋሪ ታካሚዎች በጣም ጥሩ እንክብካቤ ማግኘት ይችላሉ። ለምሳሌ፡ የአገር አቀፍ ህክምና መጠባበቂያ ከምች ከ10 ሚሊዮን በላይ የተቀመጠ ጭምብላዎች አለው። ለአህጉራዊ ህክምና መጠባበቂያ የሚሆን ጭምብላዎች ክምችት የተረጋገጠ እንዲሆን ተጨማሪ ጭምብላዎችን የአውስትራሊያ መንግሥት በማምረት በቀጣይነት እየሰራ እንደሆነ እንዲሁም ወረርሸው በቀላሉ የማይታጠፍ ስለሆነ አውስትራሊያ ለእኛ ህክምና ባለሙያዎች የሚረዳ በቂ ግላዊ መከላከያ መሳሪያ እንዳላት ነው። በዚህ የሚካተት የአካባቢ ፋክቶሪ ምርት አቅርቦት አቅምና ችሎታ ስለመጨመር ይሆናል።

በአውስትራሊያ ውስጥ በአብዛኛው ሆስፒታሎች 2,200 ንጹህ አየር መተላለፊያ መሳሪያ ያላቸው አልጋዎች እንዳሉ ነው። ባለፉት ስድስት ሳምንታት የሚያስተኛ ማደንዘዣ/ anaesthetic መሳሪያዎች እና ሌላ መሳሪያዎች በማስገባት አሁን 4,400 ንጹህ አየር መተላለፊያ ያላቸው አልጋዎች እንዳሉንና ወደ 7,500 እንዲሆን ጥረት እያደረግን ነው። በሚያዚያ/ April ወር መጀመሪያ ላይ

በከተኛ ክትትል ክፍል ውስጥ ከኮሮና ቫይረስ ጋር በተዛመደ ታካሚዎች የንጹህ አየር መተላለፊያ መሳሪያ ፈላጊዎች ቁጥር 20 እንደነበረ ነው።

አውስትራሊያ የተላላፊ በሽታ አሰራር መዋቅር በመመርመሪያ መሳሪያዎች ያለን መመሪያ እንደገና ለማበየት በየቀኑ ስብሰባ እንደሚያደርግ፤ ስለዚህ ጠቃሚ የሆነ መመርመሪያ ብቻ ይወሰዳል።

## ውሸት: በኮሮና ቫይረስ ምክንያት ጥያቄ ስለጨመረ የአውስትራሊያ ሆስፒታሎች ሊቋቋሙት አልቻሉም

**እውነት:** የአውስትራሊያ ህዝባዊና ግላዊ ሆስፒታሎች የኮሮና ቫይረስን ለመዋጋት የተባበረ ሀይል አላቸው። በአውስትራሊያ መንግሥት፤ አስተዳደር ግዛት እና ንተሪቶርይ መንግሥታትና የግል ሆስፒታል ክፍል መካከል የአጋርነት ታሪክ ለኮሮና ቫይረስ ለመዋጋት እንዲረዳ በሃገር አቀፍ 34,000 ተጨማሪ አልጋዎች እና 105,000 የህክምና ሰራተኞች እንዲፈጠር ያደርጋል።

የግል ተቋማት ለህዝባዊ ታካሚዎች የሆስፒታል አገልግሎቶችን በማቅረብ አልጋዎች፤ አቅርቦቶችንና ሰራተኞችን በማቅረብ የህዝባዊ አሰራር ዘዴዎችን ይረዳል።

እንዲሁም በህዝባዊ ሆስፒታል ረጅም ጊዜ ቆይታ ፍላጎት ላላቸው የሃገር አቀፍ አካለ ጉዳተኛ ኢንሹራንስ ፕሮግራም ተሳታፊዎች እና በእድሜ ሽማግሌ እንክብካቤ ታካሚዎች እና አጠቃላይ ፍላጎት ላላቸው ታካሚዎች ድጋፍን ያለማቋረጥ ይቀጥላል።

አጋርነቱ የሚያረጋግጠው ለአውስትራሊያ ጤና አሰራር ዘዴ የዓለም አቀፍ ደረጃ መገልገያን ማሟላት ዝግጁ ስለመሆን ማረጋገጥ እና በዚህ ወረርሽኝ ጊዜ ለታካሚዎች ህክምና እንዳስፈላጊነቱ ህክምና ላይ ያተኮረ ነው።

## ውሸት: የሁለት ሳምንት መዘጋት የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ያቆማል

**እውነት:** ለሁለት ወይም ሶስት ሳምንታት እንዳይወጡ ማገቱና ከዚያም እገታውን ማንሳትና ወደ መደበኛ ህይወታቸው እንዲመለሱ ማድረግ ለኮሮና ቫይረስ ስርጭት አያቆምም።

ለሁለት ሳምንት ብቻ መታገት የሚያመጣው ችግር የኮሮና ቫይረስ አስቀያሚ ጭንቅላት መጠነኛ ከመሆን ምናልባት ከበፊቱ በበለጠ ሞገደኛ ቁጡ ሊሆን ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች ሌሎች አገሮች እንዳደረጉት ለምን በብርድ ልብስ መታገት አልጠየቅንም ይላሉ። ለዚህ መልሱ፤ እንደ ጣሊያን፤ ስፔንና ኢራን እንዲሁም ከተሞች እንደ ቻይና ውስጥ ዉሃን ያሉ አገሮች ወረርሽኝ መጀመር ሳይሆን እኛ ከችግሩ ቀደም ብለን አውቀን ቆይተናል።

በነዚህ አገሮች ያሉ የጤና ኤክስፐርቶች ምን እንደተፈጠረ በሚያውቁበት ጊዜ፤ ኮሮና ቫይረስ ከቁጥጥር ውጭ እንደነበረና ልክ እንደ ጫካ እሳት እንደተሰራጨ ነው። ለዚህ ነው በነዚህ አገሮች ያሉ ሆስፒታሎች ከህዝቡ ጋር ሆነው ከከባድ የበሽታ ዓይነት ጋር ይታገሉ የነበረ።

በአውስትራሊያ ውስጥ መተላለፍ ከጀመረ በየቀኑ ስለሚከሰቱት አዳዲስ ጉዳዮች ቁጥር የእኛ ኤክስፐርቶች መቆጣጠሩን ይቀጥላሉ። ከዚያም ባለው መረጃ መሰረት ምክሮችን ሲያቀርቡ ይህም ለማንኛውም አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ደንቦች ወይም እገዳዎችን ማስቀመጥ። እያንዳንዱ ሰው ከወቅታዊ እገዳ ጋር መቆየት እንዳለበት መረጃ በድረገጽ፡ [www.australia.gov.au](http://www.australia.gov.au) ላይ ገብቶ ማየት።

## ውሸት: በእያንዳንዱ ላይ ምርመራ በማካሄድ የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ያቆማል

**እውነት:** ምርመራ ማካሄድ ለቫይረሱ ስርጭት አያቆምም።

እንደ ማንኛውም ቫይረስ፤ COVID-19 ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋል። ሁልጊዜ የማሕበራዊ እርቀት በማድረግ ብቻ እና ደህና ካልሆኑ የቫይረስ ስርጭትን ማቆም እንዲቻል ከቤት ውስጥ አለመውጣት።

አንድ ሰው በታየበት ምልክቶች COVID-19 መኖር አለመኖር በምርመራ ማጣራቱ እንደሚረዳን ታዲያ የበሽታውን ስርጭት እንደሚያቆምና መተላለፍንም ይቀንሳል። አንድ ሰው ስለመኖሩ ካወቅን፤ ያን ሰው ከእነሱ ማራቅ እንዲችልና ከሱ ጋር የተገናኘን ሰው መከታተል እንደምንችልና የቫይረሱ ችግር የበለጠ እንዳይተላለፍ ይቀንሳል።

ይሁን እንጂ በምርመራ ላይ የ COVID-19 ቫይረስ አለማሳየት ማለት እርስዎ ችግር ላይ ወይም ለሌሎች ችግር ላይ አይደሉም ማለት አይደለም። በቫይረሱ ከተጋለጡ በኋላ በምርመራ የCOVID-19 ቫይረስ ላይታይብዎት ይችላል ነገር ግን ምልክቶችን ከመፈጠር በፊት ነው። አንድ ቀን በምርመራ ላይታይ ይችላል፤ ታዲያ በሚቀጥለው ቀን በቫይረሱ COVID-19 ይያዛሉ። ለዚህ ነው ጥሩ የጤና ሃይጅን ማካሄእና ከማሕበራዊ ግንኙነት መራቅ እና ጠቃሚ ጉዳይ ካልሆነ ከቤት አለመውጣቱ የሚጠቅመው።

ይህ ለ COVID-19 ቫይረስ መተላለፍ ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለሌሎች በሽታዎችም ሲሆን ታዲያ የእኛን ጤና ጥበቃ አገልግሎቶች ጥያቄ እንደሚቀንስ ነው።

## ውሸት: ለምርመራ የተዘጋጁት እቃዎች ትክክል አይደለም

**እውነት:** በአሁን ጊዜ የሚካሄደው የCOVID-19 ቫይረስ ምርመራ ትክክለኛ ለሆነ ኑክሌክ አሲድ አምፕሊፊካሽን (Polymerase chain reaction (PCR)) ተብሎ የሚጠራን በመጠቀም ነው። በምርመራው የሚሳተፍ የጤና ሙያተኛ ከሰውየው ጉሮሮና አፍንጫ ላይ ጥራጊ ናሙና ይወስዳል። በአሁን ጊዜ የሚካሄዱት ምርመራዎች ሁሉ በውጭ አገር ሲካሄድ፤ በአብዛኛው በኢሮፕና በኤሽያ ውስጥ ይሆናል። በአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ የሚጠቀሙበት ብዙ የተለያዩ የመመርመሪያ ይዞታዎችና ላቦራቶሪዎች ስላሉ ታዲያ ጠቃሚ እውነታው ተመሳሳይ የምርመራ ዘዴዎችን መጠቀማቸው ነው። በዓለም ላይ የአቅርቦትና ማምረት አቅም ጥያቄ እየጨመረ ቢሆንም ከሁሉም የመመርመሪያ አቅርቦቶች ጋር በተዛመደ እጥረት እንዳለ ነው። የጸረ-ሰውነት እንክብካቤ ምርመራዎችን በተመለከተ ውጤቱ ትክክለኛ ስላልሆነ ታዲያ ለዚህ ጉዳይ ይህን ምርመራ ማካሄድ አይመከርም።

አውስትራሊያ ለኮሮና ቫይረስ ምርመራ ብቃትና ችሎታ ስለመኖር ለማረጋገጥ ጠቃሚ በሆኑ አቅርቦቶችና አማራጭ መፍትሄዎች በመፈላለግ ላይ የአውስትራሊያ መንግሥት በህዝባዊ ጤና ላቦራቶሪ አሰራር መዋቅር በኩል ከላቦራቶሪዎችና አቅራቢዎች ጋር በቅርበት እየሰራ ነው።

*ብዙጊዜ ይህንን ድረገጽ በመጠቀም ስለ COVID-19. ቫይረስ አውስትራሊያ መንግሥት ስላቀረበው ቁልፍ መረጃን ማግኘት።*

*እንዲሁም በራስዎ ቋንቋ SBS ስለ COVID-19 ብዙ የተለያየ መረጃ አለው። እንዲሁም ሞባይል ስልክ አፕስ መጠቀም እንደሚችሉና የመንግሥትን መረጃ ለመተርጎም ማውጫውን መክፈት። ለርስዎ ፍላጎት ለሚያሟላ አንዱን መፈለግ።*

*በእንግሊዝኛ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ፡ www.australia.gov.au ላይ ማየት።*